

*አዘዘው ያለው*

## ከዛፍ ሥር ወደ ጣራ ሥር

*የማነ አስማረ*

“ሁለተኛ ሴሚስተር ላይ አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) የሚሰራው አዝባ ት/ቤት ግንባታ ተጠናቀቀና ወደ አዲሱ ሕንፃችን ገባን። በአንድ ክፍል ውስጥ ከ60 በላይ እየሆንን በአራት ክፍሎች ውስጥ መማር ጀመርን።

“አልማ ወደሰራው ት/ቤት ውስጥ ስንገባ ወንበርና ጠረጴዛ ገና አልቀረበም ነበር። ይህ አላሳሰበንም። ከዛፍ ሥር ወደ ክፍል ውስጥ የመግባት ጉጉት ነው የነበረን። ወንበርና ጠረጴዛ እስኪሟላ ድረስ የሲሚንቶው ወለል ላይና ድንጋይ ይዘን እየገባን መቀመጣችን አላስከፋንም።

“ከሁሉም በላይ አዝባ ት/ቤት ስንገባ ያስደሰተን በጥገኝነት ተዘርተን ከምንውልበት ሜዳ ተላቀን “የራሳችን” የምንለው ት/ቤትና ኳስ ሜዳ ያለን መሆናችንና የባለቤትነት ስሜት ማሳደራችን ነው። የእርስ በርሳችን ፍቅርም ጠንካራ ነበር። በጋራ ያሳለፍነው ችግር ምክንያት ሳይሆንን አይቀርም፣ ተለያይተን ወደ ት/ቤት መሄድና መመለስ ደስ አይለንም። አዝባ ት/ቤት እስከ 3ኛ ክፍል ተምሬአለሁ። አሁን ግን በ2001 ዓ.ም ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ተመርቄ በግብርና ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪዬን አግኝቻለሁ።››

*መለሰ ክብረት*

“አዝባ ገብተን ትምህርት ከጀመርን በኋላ አልማ ያመጣቸው ወንበሮችና ጠረጴዛዎች አይረሱኝም። ለየት ያለ ቅርፅ ያላቸውና የሚያምሩ ነበሩ። ከዛፍ ሥር ወደ አዲስ ሕንፃ ከመግባታችን በተጨማሪ ከድንጋይ መቀመጫ ወደ ወንበር ስንሸጋገር ሌላ ደስታ ጨመረልን።

“ያኔ በአልማ የተሰሩት እያንዳንዳቸው ሦስት ክፍል ያላቸው ሁለት ብሎኮች ናቸው። አንዷ የርዕሰ መምህር ቢሮ፣ ሁለተኛዋ የመምህራን ቢሮ፣ አራቱ የእኛ መማሪያ ክፍሎች ነበሩ።

“አዝባ እስከ 4ኛ ክፍል ተምሬአለሁ። እስከ 8ኛ እና 12ኛ የተማርኩትም እዚያው ሰቆጣ በሌሎች ሁለት ት/ቤቶች ነው። ዛሬ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የግዢና የንብረት አስተዳደር (Purchasing and Material Management) የ2ኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። በ2002 ዓ.ም እመረቃለሁ። ከታናሽ እህቶቼ አንዷም የ1ኛ ክፍል ትምህርቷን በአዝባ ት/ቤት ጀምራ፣ አሁን በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ1ኛ ዓመት የሳይኮሎጂ ትምህርቷን ጨርሳ በ2002 ዓ.ም የ2ኛ ዓመት ተማሪ ትሆናለች።”



መለሰ ክብረት

**አዘዘው ያለው**

"አዝባ ት/ቤት ዛሬ ብዙ ሕንፃዎች ተጨምረውባት እስከ 8ኛ ክፍል የሚማሩባት ሆናለች፡፡ በእኛ ጊዜ ግን እስከ 4ኛ ስለነበር፣ ከ5ኛ እስከ 12ኛ በሌሎች ት/ቤቶች ነው የተማርኩት፡፡ "ዛሬ ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመርቄአለሁ፡፡ በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪዬን ይዣለሁ፡፡"

## እናት እኩያዋንና ታላቋን ...

**መለሰ ክብረት**


"እንደ አዘዘውና የማነ ጓደኞቼ በዓመት ሁለት ክፍል የማለፍ እድል ገጥሞኝ ባያውቅም፣ ትምህርቴን የጨረስኩት አንድም ጊዜ ሳልወድቅ በየዓመቱ ከክፍል ክፍል እየተዛወርኩ ነው፡፡ ስለዚህም፣ የእኔ የትምህርት እድሜና የአዝባ ት/ቤት እድሜ እኩል ነው፡፡"

**አዘዘው ያለው**

"አዝባ ት/ቤት የተከፈተችው በ1988 ዓ.ም ስለሆነ፣ በ1988 ዓ.ም የ1ኛ ክፍል ትምህርቱን የጀመረ ተማሪዋ አንድም ጊዜ ሳይወድቅ አንድ ክፍል ብቻ ቢያልፍ፣ ከዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ ሊመረቅ የሚችለው በ2002 ዓ.ም መጨረሻ ነው፡፡

"እኔና የማነ ግን ከዚህ ጊዜ በአንድ ዓመት ቀድመን በ2001 ዓ.ም ከዩኒቨርሲቲ ልንመረቅ ችለናል፡፡ ይህ የሆነውም የማነ ከ4ኛ ወደ 5ኛ፣ እኔ ደግሞ ከ5ኛ ወደ 6ኛ ክፍል በሴሚስተር ማለፍ በመቻላችን ነው፡፡

"ከ5ኛ ወደ 6ኛ ክፍል በሴሚስተር ያለፍነው ሦስት ተማሪዎች ብቻ ነን፡፡ ከሦስት በላይ ተማሪዎች በሴሚስተር እንዲያልፉ



ያሳለፍኳቸው ልዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የተቀሩት ት/ቤቶች ትዝታ የአዝባን ያህል አይደለም፡፡

“ከዛፍ ሥር ወደ አዝባ ክፍሎች ስንገባ ግን ት/ቤታችንን የሰራልን አልማ መሆኑንና ራሱን አልማንም አላውቅም ነበር፡፡ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሆነን በአማርኛ ትምህርት ስለምህፃረ ቃል ምንነት ስንማር ከምሳሌዎች አንዱ አልማ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ያኔ “አልማ ማለት፣ “አማራ አቀፍ ልማት ማህበር” መሆኑን አወቅሁኝ፡፡ ከዚያ በኋላም ት/ቤታችንን የሰራልን አልማ መሆኑን ርዕሰ መምህራችን ሲናገር ሰምቻለሁ፡፡

“አልማን ካወቅሁት በኋላ በክልላችን የሚያከናውናቸውን የልማት ስራዎችም ልገነዘብ ችያለሁ፡፡ የከተማችንን የሕዝብ ቤተ-መፃህፍት የገነባውም አልማ መሆኑን አውቅሁኝ፡፡ ከዚያም “አልማ ማለት ትምህርት ማለት ነው›› የሚል ምስል እየተቀረፀብኝ መጣ፡፡”

*አዘዘው ያለው*

“ምንግዜም ከአዕምሮዬ ውስጥ የማትጠፋ ቀዳሚዋ ት/ቤት አዝባ ነች፡ ይሁን እንጂ ት/ቤታችንን ሰርቶልን ከሜዳ ውሎ ያወጣን አልማ መሆኑን አላውቅም ነበር፡፡ በእርግጥ፣ ትርጉሙ ምን እንደሆነ አልረዳ እንጂ፣ “አልማ” የሚል ፅሁፍ ማየቴን አልረሳም፡፡

“በዕድሜ ከፍ እያልኩ ስሄድ ነው አልማን እያወቅሁት የሄድኩት፡፡ በዚያን ጊዜ እኛ ብቻ ሳንሆን አልማም ጨቅላ ነበር፡፡ ዛሬ ሁላችንም አድገናል፡፡ ከእኛ የበለጠ ግን አልማ አድጓል፡፡”

*የማነ አስማረ*

“የሰቆጣ የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ተሰርቶ በስብሰባ ላይ አልማ እንደሰራው ተነገረና፣ በዚያ አጋጣሚ አዝባ ት/ቤታችንን የሰራውም አልማ እንደሆነ ተነሳ፡፡ ያኔ ነው አልማን ያወቅሁት፡፡ የአልማ ዕድገት የበለጠ የሚታየው በእኛ ውጤታማነት ነው፡፡ ከዚህ በላይ ለዕድገቱ ማረጋገጫ የሚሆን ማስረጃ የለም፡፡ መልካም ፍሬ አፍርቷል፡፡”

አይፈቀድም ነበር፡፡ የሚገርመው ግን፣ ከሁሉም በልጠን ያለፍነው ሦስታችንም ከአዝባ ት/ቤት የሄድን ነን፡፡”

*የማነ አስማረ*


“የእኔና የአዘዘው የትምህርት ደረጃ ከአዝባ ት/ቤታችን እድሜ በአንድ ዓመት ይበልጣል፡፡ ይህ ግን አዝባ ከእኛ ታንሳለች ማለት አይደለም፡፡ ትልቅ ሆነን ትልቅ አድርገናታል፡፡ ውጤታማ ፍሬ ያፈራች እናት ት/ቤታችን ነች፡፡ ብንዘገይ ነበር ት/ቤታችንን ትንሽ የምናደርጋት፡፡ ሁኔታዎች አላመቹም እንጂ፣ ከዚያም በላይ መፍጠን እንችል ነበር፡፡”

## አልማና የአዝባ ልጆች

*መለሰ ክብረት*

“ጅማ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ፣ በአራት ት/ቤቶች ተምሬአለሁ፡፡ ሰፊውን የት/ቤት ትዝታዬን ክፍል የሚይዙት ግን በአዝባ ት/ቤት

# ዝቅ ያለ ነው
# ከፍ የሚለው



ዛሬ ለሚገኝበት መልካም ደረጃ መነሻ የሆነው አልማ እንደሆነ ያጫወተን አቶ ፀጋዬ አሳልፈውን ያገኘነው በአማራ ብሔራዊ ክልል፣ ኦሮሚያ ዞን፣ ከሚሴ ከተማ ነበር። ሙሉ ቃለ ምልልሱ የሚከተለው ነው።

ጥያቄ፡- መጀመሪያ ሥራ ከመጀመርህ በፊት ስለነበረው የግል ታሪክህ በአጭሩ ብታብራራልን?

መልስ፡- የተወለድኩት ካራ ቆሬ አካባቢ ቆሬ ሜዳ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን እዚያው ድንጋይ መዝጊያ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማርኩኝ። የመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርቴን ካራ ቆሬ ካራማራ ት/ቤትና የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃን ደግሞ አጣዬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትያለሁ። የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ውጤቴ አጥጋቢ ባለመሆኑ ወደ ቤተሰቦቼ ተመለስኩኝ። በዚህም ቤተሰቦቼ ወደ መጥፎ ተግባር ይገባል የሚል ግምት ይዘው ነበር። ራሴን ላጠፋ እንደምችል ጠረጠሩኝ።

ጥያቄ፡- የቤተሰቦችህን ሥጋት ለማስወገድ ምን አደረግህ?

መልስ፡- ራሴን አረጋጋሁና ወደ ሽቀላ ገባሁ። ለቀን አምስትና ስድስት ብር እየተከፈለኝ አረምና ቁፋሮ የመሳሰሉትን የቀን ሥራዎች መሥራት ጀመርኩ። የግንባታ ሥራ ሲገኝም እሸከማለሁ። በወር 75 ብር እየተከፈለኝም ለአንድ ዓመት መሠረተ ትምህርት አስተምሬአለሁ። ሥራ አልንቅም። ራሴን ከአቅሜ በላይ ከፍ አድርጌ አላይም። በትንሽ ገቢ ትንሽ የሚባሉትን የቀን ሥራዎች የምሠራው ራሴን ዝቅ አድርጌ በማየቴ ነው።

ጥያቄ፡- ‹‹ካለመሥራት መሥራት ይሻላል›› በሚል ነው በጣም ዝቅተኛ በሆነ ክፍያ ትንሽ የሚባሉትን ሥራዎች ልትሠራ የፈቀድከው?

መልስ፡- በእርግጥ፣ አዋዋልን ያሳምራልና፣ ካለመስራት ዝቅ ያለውን ሥራ መሥራት ይሻላል። ዋናው ምክንያት ግን ዝቅ ብለው ካልጀመሩ ከፍ ካለው መድረስ የማይቻል መሆኑ ነው።

ጥያቄ፡- አንተ ከትንሹ የቀን ሥራ ተነስተህ ምን ደረጃ ላይ ደርሰሃል?

መልስ፡- መጀመሪያ አሁን የምገኝበት ደረጃ ላይ እንድደርስ ያገዘኝን ሁኔታ ለመግለፅ እፈልጋለሁ። ይኸውም፣ የቀን ሥራ በመሥራት ላይ እንዳለሁ አማራ አቀፍ ልማት ማህበር ከሚሴ ላይ የሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤት ከፈተ። ከየወረዳው ወጣቶች ተመልምለው በነፃ ሊሰለጥኑ ወደ አልማ ሲላኩ እኔም እድሉን አገኘሁና ገባሁ።

ለአራት ወራት በአልማ የሰለጠንነው የተሟላ ምግብና ማንኛውም የንፅህና እቃ እየቀረበልን፣ እንደ ቤተሰብ እንክብካቤ እየተደረገልን ነው። እኔ የሰለጠንኩት በግንበኝነት ነበር። በአናፂነትና በብረት ሥራ(ፌራዮ) የሰለጠኑም አሉ። መምህራኑ ትልቅ ትጋት ያላቸውና ሌላ ተጨማሪ ትምህርትም የሚሰጡን ነበሩ።

ስልጠናውን ስንጨርስ አልማ በማህበር አደራጅቶና ለሙያችን አስፈላጊ የሆኑ የሥራ መሳሪያዎችን በሙሉ ሰጥቶ ወደየወረዳችን አሰማራን።



በአልማ ለወጣቶች መሠረታዊ የኮንስትራክሽን ሙያ ስልጠና ሲሰጥ

**ጥያቄ፡- ወደየወረዳችሁ ኬዳችሁ በኋላ በሰለጠናችሁበት ሙያ ልትሰሩበት ችላችኋል?**

መልስ፡- ወረዳችን የግንባታ ጨረታ ሲኖር ከሌሎች ኮንትራክተሮች ጋር ያጫርተናል። የተደራጀነው አንድ ከጭቃ የተሰራ ት/ቤት በ10,000 ብር ልናድስ ኮንትራት ወስደን ከመሥራታችን በስተቀር ተስማምተን ልንቀጥል አልቻልንም። አንዳንዶቹ የሰለጠኑበትን ሙያ ትተው ወደ መምህርነት ሥራ ተሠማሩ። ወደ መከላከያ የሄዱም አሉ። ከወጪ ቀሪ ለእያንዳንዳችን 500 ብር ደርሶን ተለያየን።

**ጥያቄ፡- የአንተ እጣ ፈንታስ ምን ሆነ?**

መልስ፡- አምስት መቶ ብሬን ይዤ ወደ ከሚሴ ሄድኩና ከአክስቴ ጋር መኖርን መረጥኩ። አክስቴም ከኮንትራክተሮች ጋር እያስተዋወቀችኝና እየደገፈችኝ የተገኘውን የቀን ሥራ ሁሉ መሥራት ጀመርኩ። መጀመሪያ ለቀን 8 ብር ይከፈለኝ ነበር። ቤየጊዜው ክፍያዬ እያደገ ለቀን 20 ብር ድረስ እየተከፈለኝ ሠርቻለሁ።

በ20 ብር የሠራሁበት ፕሮጀክት ተጠናቆ ወደ ሌላ ስሄድ የቀን ክፍያው በጣም ቀንሶ ወደ 6 ብር የሚወርድበት ጊዜ አለ። ቀነሰ ብዬ ግን ሥራውን አልንቀውም። ኪሴ ውስጥ ያለው ገንዘብ እንዳይጎድል ብቻ ስለምፈልግ በስድስት ብርም እሠራለሁ።

ቀጢም የተበላ ት\ቤት ግንባታ ላይ ግን በቀን 22 ብር ይከፈለኝ ነበር። ያኔ ጓደኛ ነበረችኝ። እሷንም ይዣት ሄድኩ። እኔ በግንበኝነት ስሰራ እሷ ሻይ እያፈላች ለሠራተኞች ትሸጣለች። ፓስቲና ምግብም ታቀርብ ነበር። ከሥራ ስመለስና ወደ ሥራ እስክገባም አግዛታለሁ። እኔ ደሞዜን እሷም የምግብ ኮንትራት ክፍያዋን ስንቀበል ሃብታሞች ሆንን። የሁለታችን ተደምሮ 1,500 ብር ነው ያገኘነው።



**ጥያቄ፡- ዛሬ እንደምናይህ የሥራ ተቋራጭ ሆነህ እየሰራህ ነው፡፡ በስንተኛ የሥራ ተቋራጭነት ደረጃ ነው የጀመርከው? አሁንስ ምን ደረጃ ላይ ደርሰሃል?**

መልስ፡- ደረጃ 9 የኮንትራክተር ፈቃድ በማውጣት ነው የግል ሥራዬን የጀመርኩት፡፡ እየቀጠሩ ካሠሩኝ ኮንትራክተሮች የመልካም ሥራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀት አፅፌ ወደ ሥራና ከተማ ጽ/ቤት ስሄድ የስድስት ወር ልምድ እንደሚቀረኝና ፈቃድ ማውጣት እንደማልችል ነግረውኝ ነበር፡፡

በኋላ፣ "በአልማ ስልጥኜ የተሰጠኝ ሰርተፊኬት አለኝ" አልኳቸውና አሳየኋቸው፡፡ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስችል መልካም ሰርተፊኬት ሆኖ ስላገኙት በቀጥታ ደረጃ 9 የሥራ ተቋራጭነት ፈቃድ ሰጡኝ፡፡ በዚህም ፣ ኮንትራት ሲገኝ እየተኮናተርኩና በሰፈርም ትናንሽ ግንባታዎችን መሥራት ጀመርኩ፡፡
በመቀጠልም ደረጃዬን ወደ 8 አሳደግሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ ፒክ አፕ መኪና ገዝቼ ደረጃ 7 ደረስኩ፡፡ በዚህ ደረጃዬ በተለያዩ ቦታዎች የጤና ኬላዎችን፣ ት/ቤቶችን፣ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛዎችንና የፖሊስ



ጽ/ቤት ሠርቻለሁ፡፡ ሁሉንም ያለምንም እንከን ነው የሰራኋቸው፡፡ ከሁሉም የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሰርተፊኬት ተሰጥቶኛል፡፡

ከአንድ ዓመት በኋላ ገልባጭ መኪና ገዛሁ፡፡ ባለሙያዎችንም አሟላሁ፡፡ ከ40 እስከ 70 ለሚሆኑ ሠዎች የሥራ ዕድል ፈጥሬአለሁ፡፡ በዚህም ከደረጃ 7 በቀጥታ ወደ ደረጃ 5 ልሸጋገር ቻልኩኝ፡፡ አሁን ምድር ቤቶችና ሦስት ፎቆች ያሉት አንድ ብሎክ የኮንዶሚኒዬም ቤት እየሠራሁ ነው፡፡ አንድ ብሎክ ማለት የ28 አባወራዎች መኖሪያ ማለት ነው፡፡ ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚያስችለኝ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ነኝ፡፡

ጥያቄ፡- አሁንም የሥራ ፈቃድህን ከደረጃ 5 በላይ ለማሳደግ ታስባለህ?

መልስ፡- አዎ! ከፍተኛው ደረጃ 1 ላይ ለመድረስ ነው ፍላጎቴ፡፡ መድረስም ይቻላል፡፡ ይህንስ ማን አስቦት ነበር?


ጥያቄ፡- ሥራ ተቋራጭነት ሳታስበው በድንገት የገባህበት ሥራ ነው ማለት ነው?

መልስ፡- ግንበኝነትና ኮንትራክተርነት የሕይወቴ መሠረት ይሆናል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ፍላጎቱ ያደረብኝ





"ኑሮን በተመለከተ ቤተሰባችን ደስተኛ ነው"



*የአቶ ፀጋዬ አሳልፈውና የወ/ሮ ትዕግስት ካሳዬ መኖሪያ ቤት (ከሚሴ ከተማ)*

አልማ ካሰለጠነኝ በኋላ ነው።

በተለይም የቀን ሥራ እየሠራሁ 7,000 ብር ያህል ካጠራቀምኩኝ በኋላ ኮንትራክተር የመሆን ምኞቴ እየናረ ሄደ። በዚህ ጊዜ ከጓደኛዬ ጋር ትዳር መስርተን ስለነበርን ቤት እንድንሰራበት ትፈልግ ነበር። ፈቃድ ቢቀድም እንደሚሻል ስነግራት ግን ፈቃደኛ ሆነች።

**ጥያቄ፡- የቤተሰብህ አኗኗር ምን እንደሚመስል ልትገልፅልን ትችላለህ?**

መልስ፡- በቅድሚያ እኔና ቤተሰቤን ለተሻለ የኑሮ ደረጃ ያደረሰን አልማ ነውና ላመሰግነው እወዳለሁ። የአልማን ውለታ ለመግለፅ ይቸግረኛል ። እሱ ነው መንገዱን አሳይቶ የመራኝ። ያሳየኝን መንገድ ባለመሳቴ ሁሉም ነገር ቀና እየሆነልኝ ነው። አልማ ያሳያቸውን መንገድ ያልተከተሉና የወደቁ አሉ። አልማ አኩርቶኛል ። እኔም አደራውን ባለመብላቴ አኩርቼዋለሁ።

ኑሮን በተመለከተ ቤተሰባችን ደስተኛ ነው። እኔና ባለቤቴ ወይዘሮ ትዕግስት ካሳዬ ከገጠር እስከ ከተማ አብረን ኖረናል። መጀመሪያ የሳር ፍራሽ ላይ ነበር የተገናኘነው። አጋዤ ናት። በጋራ ነው ያደግነው። ዛሬ ጥሩ የመኖሪያ ቤት ሠርተናል። ሁለት ሴትና ሁለት ወንድ ልጆችን አፍርተን በመልካም ሁኔታ እንኖራለን።

በአልማ ጀምሬ በልምድ ያዳበርኩት ሙያየን ለማሻሻል እየተማርኩ ነው። ደሴ በሚገኝ ኢትዮ አፍሮ ሚሌኒዬም በተባለ ት/ቤት በአናፂነት ሙያ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። በዲፕሎማ ለመመረቅ አንድ ዓመት ይቀረኛል።

**ከአልማ ጋር ተደራጅተን ባለን አቅም ለልማት እንረባረብ!**

# የቴዎድሮስ ህልም

*(ከመዝሙር ፈንቴ)*

አፄ ቴዎድሮስ ለአገራቸው ከነበሯቸው መልካም ራዕዮች መካከል ጎላ ብሎና ተዘውትሮ የሚነገረው ለአንድነት የነበራቸው ቀናኢ አስተሳሰብና ጥረት ነው፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ግን፣ ወቅቱ በሚፈቅደው ደረጃ፣ የነፃ አገራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ትልቅ ራዕይም ነበራቸው፡፡ ይህ ግን በአንዳንዶች እጅግ በደበዘዘ ሁኔታ ተጠቁሞ የሚታለፍ ከመሆኑም በላይ፣ በብዙዎች ዘንድ አይታወቅም፡፡

የማይበላ የጥንታዊ አያቶቻችን አደራ እንዳለብን ስንናገር ሙሉ አፅንኦት ሰጥተን የምናነሳው የአገር ዳር ድንበርን አስከብሮ የማቆየት ጉዳይን ብቻ ነው፡፡ አብዛኛው ቀደምት ታሪካችን የጦርነት ከመሆኑ የመነጨ ሳይሆን አይቀርም፣ ከተጣሉብን ከባድ የአባቶቻችን አደራዎች አንዱ አገራዊ መሠረት ያለውና ከጥገኝነት የተላቀቀ የኢኮኖሚ ግንባታ መሆኑን እንዘነጋዋለን፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ግን የሥራ ጥበብ በአገራቸው ሰዎች እጅ እንዲገባ የነበራቸው ፍላጎት ከፍ ያለ ከመሆኑም በላይ፣ ይህ ይሆን ዘንድ ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግር ወይም የሰው ሃይል ልማት ብቻ አገራቸውን በእድገት ጎዳና ሊያራምዳት እንደሚችል በመገንዘባቸውም ከእሳቸው በኋላ ከነበሩት ነገስታት ሁሉ የላቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በቴክኖሎጂ የተራመዱት አገሮች ያፈሯቸውን የጦር መሣሪያና ሌሎች ቁሳቁሶች እየተረዱም ይሁን እየሸመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አገር ውስጥ በማስገባታቸው ብቻ፣ እስከ ዛሬም ድረስ የሥልጣኔ በር ከፋች ከሆኑ እየተቀጠረ ብዙ ታሪክ ይተርክላቸዋል፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ግን፣ የወቅቱ ሁኔታ ያልፈቀደላቸው ሆኖ ሳይሳካላቸው ቢቀርም፣ በዚያ ዘመን ተፈጥረው ቴክኖሎጂ ማለት በዋናነት አንድን ዕቃ የሚሰሩበት ተግባራዊ ብልሃት እንጂ የሌላ አገር ብልሃተኛ የሠራውን መሸመት ወይም መቀለት እንዳልሆነ አበክረው መረዳት የቻሉ ነበሩ፡፡ ለዚህም ነው፣ የእንግሊዟ ንግስት ቪክቶሪያ ዥጉርጉር ምንጣፍ በላኩላቸው ጊዜ ‹‹የአገሬን ሠዎች ጥበብ አስተምሩልኝ አልኩ እንጂ....›› ሲሉ ስጦታውን ያጥላሉት፡፡ ለእንግሊዝ ጦር መዝመት መንስኤ የሆኑትን ፈረንጆች መቅደላ አምባ ላይ አስረው ያስቀመጡበት አንዱና ዓይነተኛው ምክንያትም፣ ፈረንጅ የተባለ ሁሉ በእጅ ጥበብ የተካነ አድርገው መቁጠራቸውና ጥበባቸውን ለአገራቸው ሠዎች እንዲያስተምሩ ላቀረቡላቸው ጥያቄ እምቢታን የመለሱ ልግመኞች ስለመሰሏቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ አፄ ቴዎድሮስ ሴባስቶፖል የተሰኘው መድፋቸውን ከመሥራታቸው በስተቀር፣ ከእሳቸው አስተሳሰብ በብዙ ርቀት ወደ ኋላ የቀረው ጊዜ ሙሉ ህልማቸውን እንዲፈቱ ያልፈቀደላቸው ባለ ትልቅ ራዕይ እንደነበሩ የታመነ ነው፡፡ ተከታዮቹ ነገሥታት በማያደምቀው የሠው ወርቅ ለመድመቅ ከመሞከር ያለፈ ታሪክ አለመሥራታቸውም፣ የአፄ ቴዎድሮስ የእድገት መንገድ ጅምርና ውጥን ሆኖ እንዲቀር እንዳደረገ መናገር ይቻላል፡፡

ይህን በሰው ኃይል ልማት ላይ የተመሠረተ የዕድገት መንገድ ማስቀጠል ቢቻል በወቅቱ ከኢትዮጵያ የሚመሳሰል የእድገት ደረጃ ላይ ትገኝና የአፄ ቴዎድሮስን ዓይነት የእድገት መንገድ ትከተል ነበር ከምትባለው ጃፓን የሚስተካከል ወይም በቅርብ ርቀት የሚከተል ኢኮኖሚ መገንባት ይሳነን ነበር?

ጃፓን ምንም ዓይነት የተፈጥሮ ሃብት የላትም፡፡ የሰው ሃይሏን ለቴክኖሎጂ እድገት በሚበጅ ትምህርትና እውቀት የማደርጀት መንገድን በመከተሏ ግን፣ ከአሜሪካ ቀጥሎ ሁለተኛው የዓለማችንን ትልቅ ኢኮኖሚ መገንባት ችላለች፡፡ ይህ ነው የሚባል የተፈጥሮ ሃብት ባይኖራትም፣ የሰው ኃይሏን በእውቀት ማበልፀጓ፣ በሌላው ዓለም የተፈጥሮ ሃብት የመጠቀም ሰፊ እድል ሰጥቷታል፡፡ ለዚህም ነው፣ ከሌሎች ሃብታም አገሮች በተለየ ሁኔታ፣ ጃፓን በአገሯ ውስጥ ካፈሰሰችው መዋዕለ ንዋይ ይልቅ የውጪ ኢንቨስትመንቷ የላቀ የሆነው፡፡



ወደ አገራችን ሁኔታ ስንመለስ፣ በአሁኑ ጊዜ የአፄ ቴዎድሮስን የእድገት ራዕይ በላቀ ደረጃ እውን የሚያደርጉ አያሌ ጥረቶችን መመልከት ጀምረናል፡፡ በጥቂቶች ላይ የተወሰነ ከመሆኑም በላይ፣ ከሥራ ፈጠራና ከምርታማነት ጋር ሳይዛመድ ለዘመናት የዘለቀው ነቢባዊ የትምህርት ፖሊሲ ተሸሮ ተግባር ተኮር የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ መነደፉና ለብዙዎች ይዳረስ መጀመሩ ብቻ ለዚህ ታላቅ ምሳሌ ነው፡፡



ከመንግሥት መጠነ ሰፊ ጥረት ጎን ለጎን የተለያዩ ተቋማትና አማራ አቀፍ ልማት ማህበርን (አልማ) የመሰሉ የልማት ማህበራትም፣ ትምህርትና ስልጠናን በማስፋፋት ረገድ ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው፡፡

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር ባለፉት 18 ዓመታት በልዩ ትኩረት ካከናወናቸው የልማት መስኮች አንዱ ትምርትና ስልጠና ነው፡፡ የአልማ ፕሮጀክቶች ተፈፃሚ በሆኑበትና በሚሆኑበት የክልሉ አካባቢዎች ተዘዋውሮ የተመለከተ ሁሉ፣ በዚህ ፕሮግራም ኑሮአቸው በእጅጉ የተሻሻለና የመሻሻል ተስፋቸው የለመለመ ወገኖች እልፎች መሆናቸውን በቀላሉ ሊታዘብ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ፣ ለሁሉም ዜጋ በስፋትና በጥራት እንዲዳረስ ልዩ ትኩረት የተሰጠው የአገራችን የትምህርትና የስልጠና ዘርፍ ተከታታይ እድገት ለሚያሳየው የኢኮኖሚ ዕድገት ጠንካራ መሠረት በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ አማራ አቀፍ ልማት ማህበርም በዚህ የሰው ኃይል ልማት መስክ ያስመዘገባቸው ድሎች የኢትዮጵያም ሆነ የአማራ ክልል የልማት ህዳሴ ትልቅ አካል እንዲሆን አስችሎታል፡፡

ይህ ጥረት የዕድገት ሥልጣኔ በአገራቸው ሠዎች እጅ ትሆን ዘንድ መልካም ህልም ለነበራቸው ቀደምት አያቶቻችን ትንሳኤ ነው፡፡ አዎ! እየተፈታ ነው፣ የቴዎድሮስ ህልም!



ከዛሬዋ ጃፓን

